# “ነፃው” ፕሬስ ራሱ ለዚህስ ምን መልስ አለው?!

**ዘሩባቤል ማቲያስ** 04/30/13

አዲስ ጉዳይ መጽሔት በወርሃ ሚያዚያ ሰሞነኛ ህትመቷ የመንግስትን ምላሽ የሚሹ “የነጻውን” ፕሬስ አጀንዳዎች አስተናግዳለች፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን የአውሮፓ ጉብኝትና ከፈረንሳዩ “ፍራንስ 24” የቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ያደረጉትን ቃለ-ምልልስ ተከትሎ፤ በራሳቸው ምክንያት ሀገር ጥለው የኮበለሉ፣ ጋዜጠኝነትን ለተሻለ የህይወት አማራጭ ቪዛ ማስመቻ አድርገው የወሰዱ አሊያም ከጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር ውጪ የሀገሪቱን ህግና ስርዓት በመፃረር ሲሰሩ የነበሩ የ14 “ጋዜጠኞችን” ፎቶ እንደ አልበም ወይም እንደ ፎቶ ቤት በሽፋን ገጿ ላይ በመደርደር “መንግስት ለዚህስ ምን መልስ አለው?” የሚል ጥያቄን በማንሳት በርዕስ አንቀጿ ላይ ስለ ስደት እንዲሁም በዐብይ ጉዳይ አምዷ ላይ ጉዳዩን ይበልጥ በማራገብ ለመሞገት ሞክራለች። ዋነኛው ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለቴሌቪዥን ጣቢያው በነፃው ፕሬስ ይዞታ ላይ ተገቢውን ማብራሪያ አልሰጡም የሚል ነው–‘እኛ የምንፈልገውን ብቻ በሉልን’ የማለት ያህል።

“የጋዜጠኞች” ስደትና እንግልት እንዲቆም በማሳሰብ ወይም በማስጠንቀቅ ይጀምራል–ርዕሰ አንቀፁ፡፡ ምናባዊው የዐብይ ጉዳይ አምድ አዘጋጅ ከአምዱ ስያሜ ግርጌ ያስተናገዳቸው ባለ አራት ገፅ ዲስኩርም በተዘዋዋሪ መንገድ የመፅሔቷ አቋም የሆነው ርዕሰ አንቀፅ ማጠናከሪያ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ ዝግጅት ክፍሉ ቦታ ጠቦት ይሁን አሊያም እርካታ ባለማግኘት በውል ባይታወቅም፤ የርዕሰ አንቀፁ አባሪ ወይም ተጣማሪ ሆኖ የቀረበው ፅሑፍ መንግስትና “ነጻው” ፕሬስ በአይጥና ድመት ተመስለው እንዲታዩ ለማድረግ የተሞከረበት አምድ ነው፡፡

ግና የስውር አምድ አዘጋጁ ፅሑፍና (የዐብይ ጉዳይ አምድ) የርዕሰ አንቀፁ ድምር ውጤት አንድ ነው፡፡ እርሱም መንግስት “ነጻውን” ፕሬስን እየተጫነው፣ እያቀጨጨውና እያዳከመው መሆኑን በአንድ በኩል ሲገልፅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጋዜጠኞች እየተሰደዱና እየተንገላቱ መሆኑን ማሳየት ነው– ተሰዳጅና አሳዳጁን እግዜር ይወቀው እንጂ፡፡ ሆኖም በእኔ እምነት የአሳዳጅነቱን ሚና መውሰድ ያለበት “ነፃው” ፕሬስ ራሱ ይመስለኛል፡፡

ለፅሑፌ መነሻ የሆነኝ ዘንድ ይኸው የርዕሰ አንቀፁ አባሪ ሆኖ የቀረበው ባለ ብዙ  ንዑስ አርዕስት ፅሑፍ ዋናው ጉዳይ ረጅም ግን አጭር ወግ ነው፡፡ ከአምዱ ጀርባ ተደብቀው ብዙ ለማለት የተውተረተሩት ፀሐፊው፤ ጉዳዩን ደግመው ደጋግመው በብዕር ቢያርሱትም ቅሉ፤ ምርታማ የሆኑ ግን አይመስሉም፡፡ ጭልጥ ያሉ “የነጻው” ፕሬስ “አድናቂና አድማቂ” በመሆናቸው ቀዩ ብዕራቸው ቀያይ ንዑስ ርዕሶችን በመቀራረም (…እስር፣ እንግልት፣ “ነጻው” ፕሬስ በመንታ

መንገድ ላይ …ወዘተ) በመሳሰሉ ጨለምተኛ ቃላትና ሃረጋት የቻሉትን ያህል ለመቧቸር ሞክረዋል–የሆነ ቦታ ተደብቀው፡፡

እንግዲህ ልብ እንበል!…መፅሔቷ ለማብጠልጠል የመዘዘችው ጉዳይ ሚዛናዊነትን የደፈጠጠና ኢ- ታአማኒነት የጎደለው ለመሆኑ ሙሉ ጽሑፉን ማንበብ አያስፈልግም፡፡ ዘገባው የተዘጋጀበት አምድ ባለቤት አልባ መሆኑ በራሱ ከጀርባው ተጠያቂነትን ለመሸሽ ያደፈጠ ወይም አጥር ጥግ ቆሞ ድንጋይ ወርውሮ እንዲሚሮጥ ልጅ ሆኖ መቅረቡ በቂ ማሳያ ይመስለኛል፡፡ ለምን ቢሉ፤ የዘገባው ባለቤት ቢያንስ በብዕር ስም አሊያም እንደሌሎቹ አምዶች በስም ተጠቅሶ መቅረብ እንዳለበት ሙያው የሚያስገድደው ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ እናም ከሙያው አንፃር ማንኛውም ባለቤት የሌለው አምድ እንዲሁም የዝግጅት ክፍሉ አቋም መሆኑ ከአምዱ ግርጌ በመግለጫ ያልተጠቀሰ ገፅ የፕሬሱ አዘጋጅ አቋም ተደርጎ እንደሚወሰድ መታወቅ ይኖርበታል። ለነገሩ የጽሑፉ ባለቤት የዝግጅት ክፍሉ መሆኑን ለመገመት አይከብድም፡፡ የርዕሰ አንቀፁን ጭብጥ በመመልከት ብቻ የስውሩን "ዐብይ ጉዳይ" ፀሐፊ ማንነት ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ሆኖም የዚህ ፅሑፍ የትኩረት አቅጣጫ "መንግስት ለዚህስ ምን መልስ አለው?" ለሚለው 'እንደ ተመኘሁሽ አገኘሁሽ' ወይም 'እጇ ላይ ባለሽ' ለሆነው የጉጉ ሰው ዓይነት ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንጂ የስውሩን "አምደኛ" ማንነት ለማሰስ ባለመሆኑ ወደ ጉዳዩ ልመለስ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የፅሑፍ ባለቤት አልቦነት ችግር ራሳቸውን "ነፃ ነን" እያሉ የሚጠሩ ፕሬሶቻችን (በዓለም ላይ ያለው ነፃ የሚባል ፕሬስ ሳይሆን የግል ፕሬስ በመሆኑና ነፃነት ሁሌም አንፃራዊ ስለሆነ) "ጥፋት አንድ" ተብሎ ይመዝገብልኝ፡፡

"የነጻ" ፕሬሶቻችንን ጥራዝ ነጠቅነትን ወይም ግልብነትን የሚጠቁም አንድ ቅንጣት ነገር ግን በቂ የሆነን ማሳያን ካስቀደምን ዘንዳ የምዕናባዊውን "ፀሐፊ" ጥያቄ በጥያቄ መልሰን ወደ ዋናው ጉዳያችን እንዝለቅ፡፡ ፀሐፊው፣ "መንግስት ለዚህስ ምን መልስ አለው?" ብለዋል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ደግሞ "ነጻው ፕሬስ ራሱ ለዚህስ ምን መልስ አለው?!" እላለሁ፡፡ እንግዲህ የዐብይ ጉዳይ አምድ ባለቤት ዝግጅት ክፍሉ እንደሆነ ገምተናል ወይም ተግባብተናል። እናም ተከታዩን ጥያቄ እንጠይቀው እሱም "የነጻው" ፕሬስ አንድ አካል፣ ለዚያውም ግንባር ቀደም አቀንቃኝ ነውና፡፡ ፀሐፊው "ነጻ" ፕሬስ አደጋ እንደተጋረጠበት ደግመው ደጋግመው በመልክና በቅርጽ እንዲሁም በየትየለሌ ንዑሳን አርዕስቶቻቸው አራግበዋል፡፡ እናም እንደ አንድ ዜጋ ምላሼን ልስጥ፤ ልጠይቅም፡፡ ሃቅን መመስከር ወይም የምናስተውለውን ጠማማ አስተሳሰብ ማረቅ የማንኛውም ዜጋ ግዴታም ሆነ መብት ይመስለኛል፡፡ "የነፃ" ፕሬስ ተሟጋች አሊያም እርሳቸው ብቻ ተቆርቋሪ ሆነው በስውር የቀረቡት ግለሰብም ቢሆኑ የሚከፉብኝ አይመስለኝም– ከጽሑፋቸው እንደ ተረዳሁት በሃሳብ ፍጭት ያምናሉና፡፡ ስለሆነም የአዲስ ጉዳይ ዝግጅት ክፍል በከፊል፣ ከፍ ሲልም "ነፃው"

ፕሬስ የጋዜጠኝነት ሙያ ደፍጥጦ እንደ እርሳቸው እዚህም እዚያም ለሚረግጡ የሙያው ተገልጋዮች (አገልጋዮች አላልኩም) ምን ምልከታ ይኖረው ይሆን?...

ረጅም ሳንጓዝ የአዲስ ጉዳዩን አፍራሽ አካሄድ ለአብነት እንምዘዝ። መጽሔቷ ድብቅ የአምድ አዘጋጅ አላት፡፡ በእኔ እምነት ራሷ ለሙያው ተገዥ ሳትሆን፣ ሳትማር ሳትወቀስ ወይም ለአቅመ ሃያሲነት ሳትበቃ በራሷ ጊዜ የአዋቂነትን ዘውድ የደፋች ይመስለኛል፡፡ ወይም ደግሞ “ስጡ እንጂ ልስጥ አልኩ ወይ?” እንዳሉት የኔታ፣ ‘የሙያውን ህግ አክብሩ እንጂ ላክብር አልኩ ወይ?’ እያሉ ነው፡፡  እርግጥ የጸሐፊው አጀንዳ የሚጠላ አይደለም፡፡ መታረም የሚገባው ነገር ከተገኘ እንዲታረም ማሳሰቡም በዚያው ልክ አይከፋም፡፡ “ነፃ” ፕሬሱ ይደግ ፣ ይመንደግ ማለቱ ከአንድ የፕሬስ አካል ብቻ ሳይሆን ከመንግስትም የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ እናም አያስወቅስም፡፡ የሚያስወቅሰው፣ የሚያስተዛዝበውና የሚጎረብጠው ጉዳይ ግን የራስን ድክመት ወደ መንግስት ለማላከክ መሞከሩ ነው፡፡ ምክንያቱም “የነጻ” ፕሬሱ አለማደግ ከራሱ ከዝግጅት ክፍሉ መጀመሩ ተቋሙ ራሱን አለማብቃቱን ጠቋሚ ነውና፡፡ በሌላ አባባል “ነጻው” ፕሬስ ራሱ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለበት ባይ ነኝ። እናም ከዚሁ ጋር ተያያዥ ጉዳዮችን ላስከትል፡፡

...ውይ የኔ ነገር ረሳሁት እኮ!...ይቅርታ!... እስቲ ቀሪ ትዝብቶቼን ለጊዜው ገታ ላድረግና ቀደም ሲል በ“አልበምነት” ወደ መሰልኩት የመጽሔቷ የሽፋን ምስሎች ልመለስ፡፡ ቀለሟን አንጠፍፋ ልትጨረስ ምንም ያህል ያልቀራት የባለ ቀይ ቀለም እስክርቢቶዋ ቀፎ ከመጽሔቷ ግርጌ ተቀምጣለች፡፡ ቀሪውንና አብዛኛውን የፊት ሽፋኗን ስውር ፀሐፊው የብዕር አርበኛ (የፅሑፉ ፍካሬያዊ ፍቺ ነው) እያለ የሚያንቆለጳጵሳቸው “ጋዜጠኞች” ፎቶ አጨናንቆቷል – ልክ እንደ ማስታወሻ አልበም፡፡

...እስክንድር ነጋ፣ ክፍሌ ሙላት፣ ሲሳይ አጌና፣ አርጋው አሽኔ፣ ዳዊት ከበደ፣ ርዕዮት ዓለሙ፣ ውብሸት ታዬ...ወዘተርፈ. ሶስት በአራት (3*4) በሆኑ ፎቶዎች ይታያሉ፡፡ አንዳንዶቹ የህግ ታራሚዎች ናቸው– ፀሐፊው “አርበኛ” ቢሏቸውም፡፡ ጥቂት የማይባሉት ደግሞ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ አሜሪካና ምዕራብ አውሮፓ አቅንተዋል፡፡ በፀሐፊው አባባል መንግስትን ፈርተው ወይም መንግስት አስፈራርቷቸው የተሰደዱ የብዕር ጥመኞች ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ብዕራቸውን ከሙያው ስነ-ምግባር ውጪ ብዕራቸውን ለሁከትና ለብጥብጥ በመጠቀማቸው እንዲሁም ስራቸውን ስለሚያውቁ በራሳቸው ጊዜ ሀገር ለቀው የወጡ ናቸው።....

...ወደ ቀይ እስኪርብቶዋ ልመለስ፡፡ ቀለሟ እየተየሚጠጠ ነው፡፡ ቅላቷን በአደጋ ብንመስለው ቀለም መራቧ ደግሞ መንግስት የግሉን ፕሬስ እውነት እንደጠማው አስንድሎታል ለማለት ይመስላል፡፡... ሌላም ልገምት፡፡... ‘ፅሑፍማ በእነ እንቶኔ ዘመን አከተመ’ ወይም ሌላ... ግለሰቡ ገማች ናቸውና እኔም እንዲያ ገመትኩ– ጥቂት ነገሮችን ከእርሳቸው ልማር ብዬ።...

ለማንኛውም ወደ ጉዳዩ ተመለስኩ፡፡ በአንድ ያገጠጠ ሃቅ የምንግባባ ይመስለኛል–ከ“የተሰዳጆቹ” ፣የታራሚዎቹና የነጋዴዎቹ “ጋዜጠኞች” አድናቂ ነኝ ባዩ ስውሩ ፀሐፊ ጋር። እርሳቸው በቃልም ይሁን በምስል ያነገሷቸው የዛሬዎቹ የባህር ማዶ ከተሜዎች በመንግስት አሳዳጅነት፣ ጣልቃ ገብነትና አስጊ የስራ ሁኔታ አገር አቋርጠው ባህር ሰንጥቀው እንዳልሄዱ እኛም ፀሐፊውም እናውቃለን፡፡ እርግጥ ነው ከምስላቸው እንደምረዳው የባህር ማዶ ተድላና ፌሽታ እንደሆነላቸውና የፈለጉትን እንዳገኙ ወዘናቸው የሚያሳብቅባቸው እንዲሁም (የቅናት እንዳይመስልብኝ) ገሚሶቹ ከጋዜጠኝነት ጋር በስደት የተፋቱ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ግን ሀገር ቤት ሆነው እንደሚሰሩት ዓይነት ዘገባ ባህር ማዶም ሆነው የአሸባሪው ግንቦት ሰባት ልሳን ለሆነው ኢሳት ወይም እሳት ቴሌቪዥን አዳማቂ አዘጋጆች ሆነዋል። እርግጥ አብዛኞዎቹ አሁንም ይፅፋሉ፡፡ ግና የቅርብ ሩቅ ናቸውና ስለ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሚያውቁ ባለመሆናቸው ከዚያ እየጻፉ በወንጭፍ የሚልኩልን ማምታቻ ጽሑፍ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ፀሐፊው በአዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓችነት ክንፈራቸውን የመጠጡላቸው ግለሰቦች የአሜሪካ ኑሮ አማልሏቸው እንጂ መንግስት አስኮብልሏቸው እንዳልሆነ ራሳቸውም ቢሆኑ መስክረዋል – በጋዜጠኝንት ቪዛ ተሰጥቷቸው የተሻገሩ ናቸው በማለት፡፡

ስውሩ አዘጋጅ እንዳልከዱትና የዚህ ፅሑፍ አቅራቢም እንደሚያውቀው አንዳንዶቹ ወደ ጋዜጠኝነት ሙያ ውስጥ ዘው ብለው በድፍረት በመግባት የተከበረውንና ታላቅ የሆነውን ሙያ ለግል ጥቅማቸው ማሳደጃ፣ ለገንዘብ ማግኛ እንዲሁም የውጭ ትምህርት ዕድል ማፈላለጊያነት ምቹ ድልድይ ያደርጉታል፡፡ ዳሩ ግን ፀሐፊው ያን ያህል የነቀዘ ስብዕና ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች ሳይቀሩ ሙያውን እንደሚቀላቀሉት እያመኑ ለግለሰቦቹ ስደት ምክንያት ደግሞ መንግስትን ይጠቅሳሉ፡፡ ሁለት የሚጣረሱ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ፀሐፊው ሃቁን ለምን ለማድበስበስ እንደፈለጉ ባይገባኝም፤ የስፖርት፣ የመዝናኛ  ፕሮግራም አዘጋጆች ሳይቀሩ በመንግስት ጫና እንደተሰደዱ አድርገው ድምድመዋል ወይም ዋሽተዋል። ምክንያቱም ምናልባትም “ነጻውን” ፕሬስና መንግስትን ድመትና አይጥ አድርጎ የሚያስፈርጃቸው /መፈረጅ ግድ ከሆነ ማለቴ ነው/ የፖለቲካ ነክ ዘገባዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ፀሐፊው ለማራገብ እንደሞከሩት መንግስት የቱንም ያህል የግሉ ፕሬስ ተቃዋሚ ቢሆንም (ከባህሪው በመነሳት ሊሆን አይችልም እንጂ )፤ አንድ የልጆች መዝናኛ ፕሮግራም አዘጋጅ ከመንግስት ጋር የሚያጣላ ዘገባ የሚሰራበት ምክንያት አይኖርም–የህፃናት ፖለቲካ የለምና፡፡ ነገሩን እንጂ መንግስትና “የነፃ” ፕሬሱ ቤተሰቦች የጸባቸው መንስዔ ፖለቲካ መሆኑን እየመሰከርኩ አይደለም–ሥርዓት አልበኝነት ነው ፤ ዋነኛው የችግሩ መንስኤ– ጋዜጠኞች ስለሆኑ ሳይሆን ወንጀለኞች በመሆናቸው ብቻ፡፡

የአዲስ ጉዳዩ ቤተኛ ፀሐፊ “ጀግኖቼ” እሉለ ስለሚያወድሷቸው አንዳንዳቹ “ጋዜጠኞች” አፍረጥርጠን እንነጋገር ከተባለ፤ አንድም በጋዜጠኝነት ስም የተጠለሉ የኒዮ- ሊበራል ሃይሎች

አገልጋዮች፣ ሁለትም ሆድ- አደሮች እንጂ ለእውነት- ስለ እውነት የተጠሙ አይደሉም፡፡ አሜሪካዊነትን የናፈቁ ቅንጡዎች ነበሩም፤ ናቸውም፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ 'ለምን ምቾትን ተመኙ? አሊያም ለምን ኑሮ ተመቻቸው?' እያልኩ አለመሆኑ ይታወቅልኝ፡፡ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በያለበት ቦታ ቢደላው የደስታዬ ወሰን መጨበጫ አይኖረውም፡፡ እኔን የሚከፋኝና ልቀበለው የማልፈቅደው ጉዳይ ግን "በነፃ ፕሬስ" ስም ለምን ይነገዳል?፣ ለምንስ ይዋሻል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አልቦ ሲሆኑ ነው።

"የነጻ" ፕሬሱ መንዝዝ ከሚገባው ያነሰ እንዲራመድ የአንባሳውን ድርሻ የሚወስደው ራሱ ባለ ጉዳዩ እና በዙሪያው የተኮለኮሉ የመስኩ ተገልጋዮች ናቸው፡፡ መንግስት ፍጹምና እንከን የለሽ ነው ባይባልም፤ ስውሩ ፀሐፊ የሚያራግቡትን ያህል ዘርፉን እንዳልተጫኑነው ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ መንግስት ሚዛናዊ፣ በዕውነታ ላይ የተመሰረተንና ሙያዊ ስነ-ምግባሩን የጠበቀ ዘገባን ገንቢነቱ አንፃር የሚቀበል ይመስለኛል። አግባብነትም ያለው ነው። ጉዳዩ መንግስት አይተች፣ አይወቀስ… አይደለም፡፡ መንግስትን አስተማሪ በሆነ መንገድ መተቸት ትክክል ብቻ ሳይሆን ግድም ጭምር ነው፡፡ እርግጥ "የነፃው" ፕሬስ መድከም ለራሱም ለመንግስት ይሁን ለፕሬሱ ብሎም ለሀገሪቱ ጥሩ ዜና እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡

ይሁንና የፀሐፊው አካሄድ መንግስት ችግሮች እንዳለበትና ችግሮቹን እንዲያርም ለመጠቆም ከመጓጓት የመነጨ አይደለም፡፡ የዜግነትና የሙያ ግዴታቸውንም ለመወጣት እንዳልሆነም ለመገመት አይከብድም፡፡ እናም የመንግስትን መልክ በማጠልሸት የግል ወይም የቡድን አጀንዳቸውን ከጫፍ ለማድረስ ካልሆነ በስተቀር፣ የመማርና የማስተማር በጎ ሃሳብ አላቸው ለማለት አያስደፍርም። እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ቢኖራቸው ኖሮ ሚዛናዊነትን ወይም ተቀራራቢነትን ባስነበቡን ነበር፡፡ ግና ይህ አልሆነም፡፡ እንዲያውም ይባስ ብለው በተገላቢጦሽ ማንነታቸውን ደብቀው በመስኮት በኩል ያሻቸውን ያህል ለመናገር ነው የፈለጉት፡፡ ግና ምን ዋጋ አለው?...ሃሳባቸው አንድን ወገን በግርድፉ የሚያጠለሽ ብቻ ስለሆነ ሚዛን አልደፉም–እናም አላዳመጥናቸውም፡፡

ለግል ፕሬሱ አለመበልጸግ ራሱ ዋነኛ ባለ ጉዳዩና በመስኩ የተሰማሩ ግለሰቦች መሆናቸውን ልቦናቸው እያወቀውና በመጠኑም ቢሆን በፅሑፋቸው እየነገሩን፤ እኛ በገሃድ የምናውቀውን በገደምዳሜው አድበስብሰው ማለፋቸው ብሎም ጥፋተኛ፣ ሀገር የከዱና ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን ከፍ ከፍ ማድረጋቸው ፅሑፋቸው ጨዋነትም ሆነ ምክንያታዊነት ያንሰዋል፡፡ እንዲያውም እርሳቸው የሚያደንቋቸውን "ጋዜጠኞች" ይባስ ወደ ገደል የሚከታቸው ይመስለኛል፡፡… እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ፅሑፉ ለመማርና ለለውጥ የተዘጋጀ ከሆነ አካፋውን አካፋ ማለት በተገባቸው ነበር፡፡ "የነፃ" ፕሬሱ ቤተሰቦችን የሙያ ግድፈቶች ለማረም መትጋቱ በወሳኝነት የመስኩ መሆኑንም በተረዱት

ነበር፡፡ እርግጥ የነፃ ፕሬሱ ማበቡ ለዴሞክራሲው ሥርዓት ግንባታ የማይተካ ድርሻ አለውና መንግስትም ቢሆን ትኩረት አልነፈገውም፡፡ ለፕሬሱ ህገ - መንግሥታዊ ዋስት መስጠቱና በተግባር እንዲከወን ማድረጉ እንዲሁም በሙያው ውስጥ ተጠያቂነትና ግልፅነትን የሚያሰፍን ህግና ደንብ ማበጀቱ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመንግስት ጥረት ነው፡፡

ሆኖም መንግስት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ መጎልበት የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ ብሎ የጠበቃቸው የግል ፕሬሶች "የት ይደርሳል የተባለ በሬ…" እንደተባለው ስማቸውና ምግባራቸው ለየቅል ሳይሆኑበት የቀሩ አይመስለኝም። ብዙዎቹ "የነፃው" ፕሬስ አካላት የውድቀታቸውን መንስዔ በማጤን በቅተው የሚገኙበትን አሰራር በመዘርጋት ፈንታ በተራ አሉባልተኛ ነገሮችን በማጯጯህ ላይ የተጠመዱ ናቸው፡፡ ዋነኛ ስራቸውን ዘንግተው የመንግስትን ስም በከንቱ በማጥፋት ዘመቻ የተሰማሩ ናቸው– ጭፍን ጥላቻ። ታዲያ ይህም ሆኖ ነፃው ፕሬስ አንድ ሺህ አንድ ሙያዊ ተግዳሮቶችን ታቅፎ የውድቀቱ ተጠያቂ መንግስት መሆኑን ሊነግረን ይቃጣዋል፡፡ ለምን ዛሬም "ዓይናችሁን ጨፍኑና እናሞኛችሁ" እንደሚባል አይባኝም፡፡ እኔ እስከምረዳው ድረስ ህዝብን መዋሸት አይቻልም–- ቢያንስ ከአንድ ጊዜ በላይ ህዝብን ማታለል አይቻልም፡፡ ብዙዎቹ የግል ፕሬሶቻችን ሊዋሹን የሚከጅሉት ግን በቀያችን ያለውን ሃቅ ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው ባህር ማዶ የሚሻገሩት ጋዜጠኞች ብቻ አይደሉም፡፡ የቤት ሠራተኞች፣ ሃኪሞች፣ መሃንዲሶች፣ "አሸባሪ ፖለቲከኞች" ጭምር ናቸው፡ ይህ ሃቅ ባለበት ሁኔታ ጋዜጠኝነትን በመነጠል የመንግስት ተጠቂ አድርጎ አቧራ ለማስነሳት መሞከር አዋጭ ስልት አይመስለኝም፡፡ ምናልባት ስውሩ ፀሐፊ ጋዜጠኞች የመንግስትን የአሰራር ግድፈቶች እየነቀሱ ችግሮችን ለህዝብ ለማድረስ የሚያስችል አቅምም ሆነ ዕድል አላቸውና መንግስት ገመናው እንዳይጋለጥበት በመፍራት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጣልቃ እየገባ ጋዜጠኞች እንዲሰደዱ ሊያስገድዳቸው ይችላል የሚል ግምት (የሳይሆን አይቀርም ድምዳሜ) በተደራሲያን ዘንድ ለማስረጽ አስበው ከሆነ እሳቤው ብዙም የሚያስኬድ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ምንም ዓይነት ተጨባጭ ማስረጃ ሊኖራቸው ስለማይችል ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ዛሬ "ነፍጥ ካነሳ፣ ብዕር ያስገሳ" የሚባልበት ዘመን እንዳልሆነ ድብቁ ፀሐፊ የሚገነዘቡት ይመስለኛል– ቢያንስ በልቦናቸው። ዘመኑ በስራ የሚታመንበት እንጂ በብዕር የምንምታታበት አይደለም፡፡ ተመራጩና ተደማጩ ሃቅ የትኛው እንደሆነ መዝኖ ለመለዬት ህዝቡ ራሱ ሰፊ ዕድል ያለው መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። እናም ፈራጁና መዛኙ ህዝብ እንኳንስ የሀገራችንን ሚዲያዎች ቀርቶ መንግስትንም በመቅደም አዋጪ የሆነና ያልሆነን ጉዳይ እያመዛዘነ ለመንግስትም ምክር እየለገሰ ነው፡፡

እናም ፀሐፊው እንደ ልጅ አሊያም ጅል በመቁጠር ሊያጭበረብሩን ሞክረዋል፡፡ ባህር ማዶ የሚገኙትን ግለሰቦች "የነፃ" ፕሬስ አፈና ሰለባ ወይም በእርሳቸው አጠራር "የእውነታ መናኝ"

እንደሆኑ አስበናቸው ‘ውይ በሞትኩት! እኔን ውጪ ሀገር ይውሰደኝ!’ በማለት እንድናዝንላቸው (እንድናዝንባቸው ልበል ይሆን?) የጓጉ ይመስላሉ–“እኔን ያጓጓኝና” አሉ ጎረቤታችን አቶ ምስግና። እርግጥም በምስልም ሆነ በቃል ታላቅነታቸው ደምቆ በቀረቡት ሰዎች እንድናዝን ፈልገዋል– ሀገር ልሂቃኗን አጣች እንድንል፡፡ እኔን ድብቅ፣ሽሽግ ያድረኝና ሰውሩ ዘጋቢ አዝነንም ዝም እንድል የፈለጉ አይመስልም። እርሳቸው በመንግስት ላይ ያቀረቡትን የመረረ ስሞታ ከተቻለ በሃሳብ፣ ካልተቻለም በተግባር እንድንቀላቀል ሳይከጅሉ አይቀርም፡፡ መቼም ሴረኛ ብዕረኛ እንደ ልጅ ነውና ሁሉም ሰው አድናቂው ይመስለው የለ?!...አዎ! እንዲያ ነው። ሃቁ ግን ታቃራኒው ነው፡፡ በዚህ ፀሐፊ እምነት “የነፃው” ፕሬስ ተወዳጅ ነን ባዮቹ (ይቅርታ ናቸው ተባዮቹ) የማዶ ሰዎች ኢትዮጵያዊ ናቸውና ከሀገር በመራቃቸው የምንደሰት ባይሆንም፤ የምናዝንላቸውን ያህል የምናዝንባቸውም እንዳሉ መካድ አይቻልም፡፡

በሃፍረተ- ምግባራቸው ከምናዝንባቸው ከስውሩ ፀሐፊ ወይም ከመፅሔቱ “ታላላቅ ሰዎች” መካከል አቶ አርጋው አሽኔን እናስቀድም፡፡ ሰውዬው ለአሜሪካ መንግስት በመሰለል መረጃዎችን ሲያቀብሉ የነበሩ ግለሰብ ናቸው። ጨዋነት እንዳይጎድለኝ እንጂ በ‘ባንዳነትም’ ልንመስላቸው እንችላለን፡፡ በሀገራችን ውስጥ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ጋዜጠኞች ማህበር ሊቀመንበር ሆነው ሲሰሩ የነበሩት እኚህ ጋዜጠኛ ለአሜሪካ ኤምባሲ መረጃ እንደሚያቀብሉ የገለፀው የአሜሪካን ምስጢራዊ ሰነዶችን እየበረበረ ይፋ የሚያደርገው “ዊኪሊክ” የተሰኘው የመረጃ መረብ ነው። ይሁንና መረጃው ይፋ ከሆነ በኋላም ቢሆን የሀገራችን መንግስት ታጋሽና ሆደ ሰፊ ነውና አቶ አርጋውን ምንም አላላቸውም። ሆኖም ግለሰቡ የገዛ ህሊናቸው ኮርኩሯቸውና የሰሩትንም ስለሚያውቁ የት እንደሄዱ አይታወቅም።

ምንም እንኳን ከስውሩ ፀሐፊ የበለጠ ባለውቅም ሀገርን አሳልፎ ከመሸጥ የከፋ ክፋት በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም፡፡ እንግዲህ ፀሐፊው ወይም የዝግጅት ክፍሉ ይህን ቅሌት ገሸሽ አድርገው ነው እውነቱን ለማምታታት የታተሩት። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን ይህ መታበይ ነው፤ ህዝብንም መናቅ፡፡ እናም አቶ አርጋው ባህር ማዶ የተጓዙት (በፀሐፊው አባባል የተሰደዱት) መንግስት ስላስገደዳቸው አይደለም፡፡

እርግጥ የአርጋው አሽኔን ፈለግ የተከተሉ በርካታ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የእርሱን ያህል የመረረ ፀረ - ኢትዮጵያዊ አቋም ባይኖራቸውም። የብዙዎቹ ኮብላይ ጋዜጠኞች ዳራ ሲጠና በጋዜጠኝነት ሙያቸው ሳይሆን ህግና ስርዓትን ደፍቀው ባከናወኑት ድርጊት ተፈላጊ ወንጀለኞች የነበሩ ናቸው፤ ወይም ነበሩ፡፡ ለምን ቢሉ በወንጀለኛነት ተከስሰው የህግ ታራሚ የሆኑም አሉና፡፡ ታዲያ ይህን በመገንዘብ ቀድመው ሀገር የከዱ ናቸው እያልኩ ነው፡፡ ፀረ - ብሔር፣ ፀረ - መንግስትና ፀረ - ህገ - መንግሥት እንዲሁም ፀረ- ኃይማኖትን የሚያራግቡ ኢ-ስነ-ምግባራዊ

የነበሩ ጋዜጠኞች ናቸው፡፡ ይህ የጥፋት ማዕቀፍ ደግሞ የዛሬው የግንቦት 7 ልሳን የሆነው የኢሳት (እሳት) አገልጋይ የሆነውና የያኔዋ ኢትዮጵ ጋዜጣ (በቅንፍ ውስጥም ቢሆን ነፍስ ይማር ብለናል!) ጋዜጠኛ የነበረውን ሲሳይ አጌናን ያካትታል፡፡ እንግዲህ የአዲስ ጉዳይ መፅሔት ዝግጅት ክፍል የማያንቆለጳጵሳቸው አነዚህን በሰሉን የጥፋት ሱሰኞችን ነው።

በዚህም አለ በዚያም ግን የብዙዎቹ "ጋዜጠኞች" ዋነኛ የስደት ምክንያት "ስራቸው" መሆኑን ቢያንስ ፀሐፊው ዓይናቸው ላይ የጋረዱትን ጥቁር መሃረብ አስወግደው ማየት ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ ሀገርን በይፋ የከዳ እንዲሁም በሀገሪቱ ህግ መሰረት በአሸባሪነት የተፈረጀን ድርጅትን የተቀላቀለን ግለሰብ "በነፃው" ፕሬስ ስም ጀቡኖ ማንቆለጳጵስ መፅሔቱ ምን ዓይነት አጀንዳ እያራመደ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ስለማይሆን ነው። ምንም እንኳን በመፅሔቱ ላይ ፎቷቸው የተኮለኮሉትን ግለሰቦች የስደት አሊያም የወንጀል መንስኤን ከቦታ ውስንነት አንፃር ማንሳት ባይቻልም፤ ኪሳራና የራሳቸው ህሊና አስገድዷቸው ብሎም ከህግ ተጠያቂነት ለማምለጥ በርግገው ሁር የሸመጠጡ የመፅሔቱ "ጀግኖችን" ለአብነት ያህል ልጥቀስ– ዳዊት ከበደንና በፍቃዱ ሞረዳን፡፡

ከቅንጅት ነውጠኛ አመራር ጋር ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ ክስ ለሁለት ዓመት እስር ቤት የነበረውና ኋላ ላይም መንግስትን ይቅርታ ጠይቆ ከእስር የተለቀቀው አቶ ዳዊት፤ እንደማንኛውም ዜጋ የጋዜጣ ፈቃድ አውጥቶ አውራምባ ታይምስ የተባለ ጋዜጣን በሚያዘጋጅበት ወቅት የፀረ-ሰላም ሃይሎችን አጀንዳ በማራገብ፣ አለፍ ሲልም የአሸባሪውን ግንቦት ሰባት አባላትን በጋዜጣው ላይ እያተናገደ ሁከትን ዳግም ለማራገብ ጥረት ሲያደርግ የነበረ ነው። መንግስት ግን እነዚህን ሁሉ ህግና ስርዓትን የተላለፉ ተግባራትን ሲያከናውን ምንም አላለውም። በስተመጨረሻ ግን በኪሳራ ምክንያት ከሀገር ሊሰደድ ችሏል። የደርግ ስርዓት መቶ አለቃ የነበረው በፍቃዱ ሞረዳም ቢሆን፤ የስርዓቱን ሽንፈት ቁጭት በወረቀት ላይ ለማስተንፈስ ጦማር የሚባል ጋዜጣን መስርቶ ሲሰራ የነበረ ግለሰብ ነው። ኋላ ላይ ግን በሰራው የወንጀል ተግባር በህግ አካላት ሲፈለግ በኬንያ በኩል ፈርጥጧል። ያም ሆነ ይህ ግን ለእኔ አዲስ ጉዳይ መፅሔት ሀገር ውስጥ ህግና ስርዓትን ተከልሎ እየሰራ ለምን በጋዜጠኝነት ስም ወገ ውጪ የሚወጡ ግለሰቦች፣ የወንጀለኞች፣ የአሸባሪ ድርጅቶች አባላት ጠበቃ ሊሆን እንደቻለ በፍፁም ሊገባኝ አልቻለም።

እናም የማዶዎቹ ጋዜጠኞቻችን ስደት ምክንያቱ ሲጠቃለል ዳቦ ፍለጋ፣ በራስ ምናብ ውስጥ የሚመላለስ የተጠያቂነት ስሜትና ወንጀለኝነትን ሽሽት ነው፡፡ ድብቁ ፀሐፊ አንቶኔ ጋዜጠኝነት በወንጀለኝነት እንደሚያስጠይቅ፣ ለእንግልት እንደሚዳርግ...ወዘተ. ተናግረዋል፡፡ አጎሳቋዩም ሆነ አሳዳጁ መንግስት መሆኑ ነው፡፡ እርግጥ ነው ሙያው የህግ ተጠያቂ ከመሆን አያድንም – ጋዜጠኛ

እንደማንኛውም ዜጋ ሰው ነውና፡፡ ሰው ደግሞ መላዕክ አይደለም፡፡ ያጠፋል፤ይሳሳታል። ጋዜጠኛም ይሁን ሃኪም አሊያም የኔ ቢጤው መደዴ ሰውም ይሁን ባለስልጣን ህግን አስከተላለፈ ድረስ መጠየቁ ያለና የነበር ነው፡፡ መዳን የሚቻለው ህግና ህግን አክብሮ በመስራት ብቻ ነው፡፡

በጋዜጠኝነት ስም ፀረ - ህዝብና ፀረ -ሀገር ተግባራትን ሲያከናውኑ የተገኙ በመጠየቃቸው ስውሩ ሰውዬ እንዳሉት የግሉ ፕሬሱ ምኑ እንደተነካበት አይገባኝም፡፡ ፕሬሱ ወንጀሉን ሳይሆን ሰላምን፣ ጥፋትን ሳይሆን ልማትን ይፈልጋል – በመርህ ደረጃ፡፡ ትክክለኛውን መስመር የተላለፉና ሙያው ከሚፈቅደው አሰራር ያፈነገጡ መጠየቃቸው አግባብ ብቻ ሳይሆን ግድም ነው፡፡ እናም መንግስት ህግና ሥርዓትን የማስከበር መብትም ሆነ ግዴታ እንዳለበት ለፀሐፊው ማስገንዘብ የሚያስፈልግ አይመስለኝም– ሊቅ ይመስላሉና። እርግጥ ፀሐፊው ሃቁን ለመመስከር ፈሩ ወይም ክህደት አማራቸው እንጂ፤ የወንጀለኞች ተጠያቂነት "ከነፃ" ፕሬስ ጥሰት ጋር የሚያስተሳስረው አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡ እንዲያውም ለወንጀለኞች መሟገት ከሀገርና ከህዝብ እውነት መነጠል ነውና የሰውዬው አካሄድ ትክክል አይደለም ። ትክክል አለመሆን ብቻ ሳይሆን፤ ኢ-ሞራላዊና ኢ- ሥነ -ምግባራዊም ነው – ለምን ቢሉ ማንኛውም ፕሬስ ፀረ ሀገርና ፀረ-ህዝብ አይደለምና፡፡

እስቲ እስክንድር ነጋን፣ ርዕዮት አለሙንና ውብሸት ታዬን በአብነት ላክል፡፡ ሶስቱም ግለሰቦች ወንጀለኝነታቸው በህግ ተረጋግጦ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ናቸው፡፡ ፀሐፊው ግን ጋዜጠኛ በመሆናቸው ብቻ እንደታሰሩ እየተናገሩ ወይም እየመሰከሩላቸው ነው፡፡ እርግጥ የፍትህ ሥርዓቱን አለማመን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ስውሩ ሰውዬ ስሜታቸው ፈንቅሏቸው አሊያም ያለስራቸው ዘብጥያ ወረዱ ማለትም ይችላሉ፡፡ ግና ሁሉንም መጠርጠርና ጭቃ ለመቀባት መሞከር ግን የሚያሳፍር ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግለሰቦቹ ሰዎች በመሆናቸው ሊያጠፉ ይችላሉ ብሎ መጠርጠር ቢያንስ የአባት ነው፡፡ ጋዜጠኛን እንደ መላዕክ አስተዋይ፣ ቅንና እንከን አልባ ... አድርጎ ለማምታታት መሞከር አያዋጣም፡፡ ለራሱ "ለነፃ" ፕሬሱም ሆነ ለሀገሪቱ አይበጅ፡፡ እናም መሳሳት ተፈላጊ ነገር ባይሆንም ሰዋዊ ባህሪ ስለሆነ፤ እንዲያው በደፈናው መንግስት ጋዜጠኞችን በማንገላታት፣ በማዋከብና በማሰር ነፃ ፕሬስን እያቀጨጨው መሆኑን በመጥቀስ በጭፍን ጥላቻ ለመክሰስ መሞከር ኢ- ሳይንሳዊም ኢ- ምክንያታዊም ነው– እሳቤው ቢያንስ ሰው ሲሳሳት የሚችል ፍጡር መሆኑን አይቀበልምና፡፡ እናም የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ይጠይቃልም– "ነፃ" ፕሬሱ ራሱ ለዚህስ ምን መልስ አለው?...

እስቲ ለማንኛውም ለፅሑፌ ማጠቃለያ የመረጥኩትን የስውሩን ፀሐፊ ንፁስ ርዕስ ላስከትል። እርሳቸው "ነብይ በሀገሩ አይከበርም" ባይ ናቸው። ሀገራቸው ልሂቃንን የመመልከቻ

መነፅር እንደሌላት የጠቁመት ፀሐፊው፤ የባህር ማዶ አዋቂዎች ግን ታላቅነታቸውን አውቀው እያወደሷቸው እንደሆነ ነግረውናል–ያለ ሃፍረት። ለአብነት ያህልም ሀገራችንን በጠላትነት ፈርጆ ሰርክ የመግለጫ ጋጋታን በሚያንጋጋው በሂዩማን ራይትስ ዎች መሸለማቸውንም ጠቅሰዋል፡፡ እርግጥ ሊሸለሙ ይችላሉ፡፡ የተቋሙን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ብንተወው እንኳን፤ ቢያንስ ሂዩማን ራይትስ ዎች የሸለመውን ሁሉ አዋቂና መልአክ አድርጎ መወሰድ በራሱ ጤነኛ አመለካከት አይደለም፡፡ ሲጀመር ታዋቂነት አዋቂነት አይደለም፡፡ ታዋቂዎችም ሆኑ አዋቂዎችም የማይሳሳቱበት አንዳችም ማስረጃ ሊቀርብ እንደማይችል እርግጠኛ ነኝ፡፡ ነገርዬው ፈረንጅ የሸለመው ሁሉ ከመልአክ እንደ አንዱ ይቆጠራል ማለትም ነውና ያስተዛዝባል፤ያሳፍራል፤ያሸማቅቃል፡፡

ለነገሩ ፀሐፊው "አውቆ የተኛ…" እንዲሉት ለመሆን አሊያም ለማምታታት ፈልገው እንጂ ሃቁን አጥተውት አይመስለኝም፡፡ ሌላው ቢቀር የአይጥ እሚኗ ድንቢጥ በመሆኗ ለሙግታቸው ታማኝ እማኝ የመረጡት ሂዮማን ራይትስ ዎች እንደ አንዳንድ የሀገራችን ጋዜጠኞች ከስሙ ጋር በማይተዋወቀው ሙያው ስር ተጠልሎ ጥፋቶችን እንደሚፈጽም እናውቃለን፡፡ ይህ አክራሪ ተቋም የኒዮ - ሊበራሊስቶች አገልጋይና ደቀ-መዝሙር ነው፡፡ ኒዮ - ሊበራሊዝም ደግሞ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ሀብት ርካሽ ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት ለመመዝበር፤ ተቋሙ የሀገራቱን ስም በሰብዓዊ መብት ስም ስማቸውን እንዲያጠፋ እንዲሁም ብድርና ዕርዳታ ሳይቀር እንዲከለከሉ እንዲጠይቅ በለስ ከቀናውም የቀለም አብዮት አስነስቶ መንግስት እንዲገለበጥና አሻንጉሊት መንግስት እንዲመሰረት ለማድረግ እንደ ረጅም እጅ ይጠቀምበታል፡፡ እናም ጋዜጠኞቻችንን በፈረንካ እየደለለ ፀረ- - ኢትዮጵያዊነትን እንዲዘምሩ አያደርግም ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ እናም ለጉዳይ ፈፃሚዎቹ ያልሸለመ፣ ለማን ሊሸልም ይችላል?...

ፅሑፌን ልቋጨው፡፡ "ነፃው" ፕሬስ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ የሆነለት ተቋም እንዳልሆነ መካድ አይቻልም፡፡ ግን ደግሞ ፀሐፊው እንዳሉት ሁሉም ነገር ለጋዜጠኞች ገደል አይደልም፡፡ መንግስትም ራሱ እንደሚያምነው ተግዳሮቶች አይታጡም፡፡ በግሌ ግን የግል ፕሬሶቻችን ራሳቸው ለአቅመ "ነፃ ፕሬስነት" የበቁ አይመስለኝም– ብዙ ይቀራቸዋል፡፡ በጭፍን ጥላቻና በጨለምተኝነት የተተበተቡ ቀያይ ብዕሮችን ያነገቡ ናቸው፡፡ ቢያንስ ቅንጣት ታህል እንኳን የመንግስትን በጎ ነገር ለመዘገብ ያማቸዋል፡፡ እርግጥ አይተቹ ወይም አይውቀሱ እያልኩ አይደለም፡፡ ጤናማነትን በተላበሰ ሁኔታ ይውቀሱ ፤ያስተምሩ፡፡ ከሁሉም በፊት ግን ራሳቸው ይማሩ፡፡ እንደ ስወሩ ፀሐፊ በደም ፍላትና በእልህ በታወረ አመለካከት ሳይሆን በምክንያታዊነት ይመኑ፤ ያሳምኑም፡፡ የወንጀለኞች ዋስና ጠበቃ ከመሆን ሀገርንና ህዝብን ያስቀድሙ። መንግስትን "ለዚህስ ምን መልስ አለው?" እያሉ ከመጠየቃቸው በፊት ራሳቸውን ይገምግሙ፤ ይጠይቁ። ሚዛናዊና ፈራጁ ህዝብም

የሚጠይቃቸው ጥያቄ አለና፣ እኔም ቀደም ሲል ለጠቀስኳቸው ችግሮቹ ‘ነፃው ፕሬሱ ራሱ ለዚህስ ምን መልስ አለው?!’ እላለሁ። ቸር ያሰንብተን፡፡